የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 23 እና 24

1. "ባለቤት ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ቢያውቅ ተግቶ በጠበቀ ነበር፤ ቤቱም እንዲቆፈር ባልተወ ነበር።" ማለቱ
ሀ) በዚያ ጊዜ እስራኤላውያንን ሌባ ያስቸግራቸው ስለነበረ ነው
ለ) ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ካላወቅን መዘጋጀት እና ቤታችንን ማዳን አንችልም ሲል ነው
ሐ) የክርስቶስ ዳግም ምጽአት መቼ እንደሆነ ስለማታውቁ ዘወትር ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ሲል ነው
መ) ሁሉም

2. "ሁለት ሰዎች በእርሻ ይኖራሉ፤ አንዱን ይወስዳሉ ሁለተኛውንም ይተዋሉ... " የሚለው ክፍል የሚያሳየው
ሀ) መንግሥተ ሰማያት በእጣ እንደሚገባ
ለ) በምግባር በሃይማኖት የጸናውን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚያገቡት፣ ያልጸናውን ወደ ገሃነም እንደሚጥሉት
ሐ) ከሁለት ሰዎች አንዱ ብቻ ሊድን እንደሚችል
መ) ሁሉም

3. "እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ኖሮ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን ስለተመረጡት እነዚያ ቀኖች ያጥራሉ። " የተመረጡት የተባሉት ...
ሀ) ምእመናን
ለ) ሁላችንም ገና ሳንወለድ ወደ መንግሥተ ሰማያት ወይም ወደ ሲኦል እንድንገባ ስለተወሰነልን፣ እድለኞች ለሆኑት ለነሱ ሲባል ቀኑ ያጥራል
ሐ) መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት ቶሎ ይወሰዱና ብዙ አይሰቃዩም ፤ ሌሎቻችን ግን በስቃይ በምድር እንቆያለን
መ) ሁሉም

4. "ነገር ግን በዚያ ወራት ለፀነሱና ለሚያጠቡ ወዮላቸው " የተባለው
ሀ) የፀነሱት መንገድ ላይ ስለሚወልዱ የተወለዱት መንገድ ላይ ለመመገብ ስለሚያስቸግሩ
ለ) ኃጢአትን በሐልዮ ፀንሰው፣ በነቢብ ወልደው፣ በገቢር ለሚያሳድጉ መከራ ነፍስ አለባቸውና
ሐ) ምእመናንን በትምህርት ፀንሰው፣ በትምህርተ ወልደው፣ በትምህርት ለሚያሳድጉ መከራ ሥጋ አለባቸውና
መ) ሁሉም

5. የዓለም ፍጻሜ ምልክትን በጠየቁት ጊዜ ጌታ ከነገራቸው ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ብዙ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ይለውጣሉ
ለ) ስለ ጌታ ስም በሰው ሁሉ ዘንድ የተጠላን እንሆናለን
ሐ) ፍቅር በብዙዎች ዘንድ ትጠፋለች
መ) ወንጌል በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ ትነገራለች

6. ጌታ ለሐዋርያት ስለ ጎልፈተ ዓለም የነገራቸው በየት ተቀምጠው ሳለ ነበር?
ሀ) በደብረ ታቦር ለ) በደብረ ዘይት ሐ) በቤተ መቅደስ መ) በጥብርያዶስ ባሕር

7. "ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም " የተባለው
ሀ) በጥሪስ በ70 ዓ.ም. ቤተመቅደሱ እንደሚፈርስ ሲናገር ነው
ለ) ሕንጻ እግዚአብሔር የሆነ ሰው ይፈርሳል፣ ይበሰብሳል ሲል ነው
ሐ) ፈሪሳውያንን ለማስቆጣት ነው
መ) ሀ እና ለ

8. ጌታ ራሱን ከመሰለባቸው መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ዶሮ ለ) እርሻ ሐ) ሐሳዊ መሲህ መ) ከ ሀ በስተቀር ሁሉም

9. "በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ " ሲል
ሀ) አባቶቻችሁን አታክብሩ ለማለት ነው
ለ) አባታችሁ አንዱ ሰማያዊ ከርስቶስ ሲል ነው
ሐ) ለጣዖት ስገዱ የሚል አባት አይኑራችሁ ሲል ነው
መ) አባትን ከማክበር እግዚአብሔርን ማክበር ይበልጣል ሲል ነው
ሠ) ከ ሀ በስተቀር ሁሉም

10. ከሚከተሉት ስለ ጻፎችና ፈሪሳውያን እውነት ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ሥራቸውን ሁሉ ለታይታ ይሠራሉ
ለ) በገበያ ሰዎች እጅ እንዲነሷቸውና መምህር ሆይ እንዲሏቸው ይፈልጋሉ
ሐ) ምጽዋት ሲሰጡ መለከትን ያስነፋሉ
መ) መልሱ የለም

11. "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአብ ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ፣ ወልድም ቢሆን የሚያውቃት የለም" ማለቱ
ሀ) አብን ከፍጡራን እንጂ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ መለየቱ አይደለም
ለ) ወልድ ቅድመ ተዋህዶ የነበረን አላዋቂ ሥጋን እንደተዋሐደ ለማጠየቅ ነው
ሐ) አብ ቢያውቀውም ወልድ ስለማያውቀው ነው
መ) ሀ እና ለ

12. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምጽአቱን በምን መሰለው?
ሀ) እንደ ሌባ አመጣጥ ለ) እንደ በለስ መለምለም ሐ) እንደ ክረምት ዝናብ መ)እንደ ሰንበት ቀን

13. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሽሽታችን መቼ እንዳይሆን እንድንጸልይ አዘዘን?
ሀ) በክረምት ለ)በሰንበት ሐ)በጸደይ መ) ሀ እና ለ

14. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢየሩሳሌምን ለማዳን ያደረገውን ጥረት በምን ገለፀው?
ሀ) በተለሰነ መቃብር ለ) በትንኝ ሐ)በግመል መ) ዶሮ እና ጫጩቶቿ

15. በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 "ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም"
ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለምንድን እየተናገረ ነበር?
ሀ)ስለ ቤተመቅደስ መፍረስ ለ)ስለ ራሱ ሞት ሐ)ስለ በለስ መ) ለ እና ሐ

16. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለዳግም ምጽአቱ በተናገረበት ጊዜ እርሱ ይድናል ብሎ የጠቀሰው ምን ዓይነቱን ሰው ነው?
ሀ) እርስ በእርሱ ሚጣላውን ለ)ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለውን
ሐ) እስከመጨረሻ የሚታገሰውን መ)በደብረ ዘይት ሚኖረውን

17. ጸሓፍት እና ፈሪሳውያን የመበለቶችን ገንዘብ እንዴት ይበላሉ?
ሀ) አሸንክታባቸውን በመዘርጋት
ለ)ጸሎት በማብዛት
ሐ) በክብር ቦታ በመቀመጥ
መ)ሁሉም

18. ከሚከተሉት ውስጥ ጸሓፍት ፈሪሳውያን የሚያደርጉት የቱን ነው?
ሀ) በምኩራብ በፊተኛው ወንበር ይቀመጣሉ
ለ) የልብሳቸውን ዘርፍ ያሳጥራሉ
ሐ) በማዕድ ጊዜ ዝቅ ባለ ስፍራ ይቀመጣሉ
መ) ሁሉም

19. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸሓፎችና ፈሪሳውያንን በምን መሰላቸው?
ሀ) ትልቅ ሸክም የሚያሸክሙ ግን በጣታቸው የማይነኩት ሰዎች ለ) የተለሰኑ መቃብሮች
ሐ) ሀ እና ለ መ) የነብያት ወዳጆች

20.ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን ስለጸሓፎችና ስለፈሪሳውያን ምን መከራቸው?
ሀ) እንዳይሰሟቸው ለ) እንደሥራቸው እንዳያደርጉ ሐ) የሚያዝዙአቸውን እንዲያረጉ መ) ለ እና ሐ